# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
# The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org

## የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤን አከባበር።

፩. በዋዜማው ከምሽቱ አሥራ ሁለት ተኩል ሲሆን በዓሉን የሚያበሥር  የደወል ድምፅ ይሰማል።

፪. ልክ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ሲሆን ሥርዓተ ማሕሌቱ ይጀመራል።

ሀ) የማሕሌቱ ሥነ ሥርዓት እንደተለመደው
መሪው «ሰላም ለኪ...» ብሎ ይዘምራል(ያዜማል)። በማያያዝ ውዳሴ ማርያም፦
ተሰመይኪ ፍቅርተ ብሎ ይዘምራል።

ለ) የዕለቱ ውዳሴ ማርያም ካለቀ በኋላ፦ ጸሎታ ለማርያም ይዘመማል (በኅብረት)።

ሐ) ዲያቆን የእለቱን ምስባክ፦«ወተንሥአ እግዚአብሔር» የሚለውን ይዘምራል(ያዜማል)

## ወተንሥአ እግዚአብሔር

| | |
|---|---|
| ወተንሥአ እግዚአብሔር ከመ ዘንቃሕ እምንዋም<br>ወከመ ኃያል ወሃደገ ወይን<br>ወቀተለ ጸሮ በድህሬሁ። | እግዚአብሔር ከእንቅልፍ እንደሚነሳ ተነሳ<br>የወይን ስካር እንደተወው እንደ ኃይለኛም ሰው<br>ጠላቶቹንም በኋላቸው መታ። መዝ. ፸፯፡ ፷፭ |

በማያያዝም ቄሱ ፬ቱን ወንጌላት ያነባል።(፬ተኛው ለቅዳሴ ይቆያል)።
ዘማቴዎስ ፳፰:፩ ዘማርቆስ ፲፮:፩ ዘሉቃስ ፳፬:፩

መ) መሪ ፦«አርያም ቀዳሚ ዜማን» ይመራል ከተዘመመ በኋላ አያይዞ «ይገብሩ በዓለን»
ይመራል፣ይዘመማል።

## አርያም ቀዳሚ ዜማ

| | |
|---|---|
| ሃሌ ሉያ ለአብ ሃሌ ሉያ ለወልድ ሃሌ ሉያ ለመን ፈስ ቅዱስ፤ ቀዳሚት ዜማ ግበሩ በዓለ በትፍሥሕ ት እስከ አቅርንቲሁ ለምሥዋዕ ዛቲ ፋሲካ ቀዳሚ ት ሕግ | ለአብ ምስጋና ይገባል ለወልድ ምስጋና ይገባል ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይገባል፤ መጀመሪያዪቱ ምስጋና እስከ መሰዊያው ቀንድ ድረስ በደስታ በዓልን አድርጉ፤ ይችም ፋሲካ የመጀመሪያዪቱ ሕግ ናት። ዘዳግም ፲፮፡ ፩-፯   መዝ ፻፯፡ ፳፯-፳፰ |

## ይገብሩ በዓለ

| | |
|---|---|
| ሃሌ ሉያ ለአብ ሃሌ ሉያ ለወልድ ሃሌ ሃሌ ሉያ ወለመንፈስ ቅዱስ፤ ይገብሩ በአለ ሰማያት ይገብሩ በዓለ ደመናት፤ ወምድርኒ ትገበር ፋሲካ ተሐጺባ በደመ ክርስቶስ | ለአብ ምስጋና ይገባል ለወልድ ምስጋና ይገባል ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይገባል፤ ሰማዮች(በሰማይ ያሉ ፍጥረታት) በዓል ያደርጋ ሉ ደመናትም በዓል ያደርጋሉ፤ ምድርም በክርስቶስ ደም ታጥባ ፋሲካን ታደርጋለች። ፩ቆሮ ፭:፯ ፡ ፩ጴጥ ፩፡ ፲፰-፲፱ |

ሠ) መሪ ምልጣን፦ «ዮም ፍሥሐ ኮነ» ብሎ ይመራል። ከተዘመመ በኋላ፦ በኅብረት እስመ ለዓለም ፦ ትንሣኤከ ለዕለ አመነ ይጸነጸላል። በዚሁ ዑደት ይደረጋል።

## ምልጣን

| | |
|---|---|
| ዮም ፍስሐ ኮነ በሰንበተ ክርስቲያን<br>እስመ ተንስአ ክርስቶስ እሙታን<br>ቀደሳ ወአክበራ እምኲሎን መዋዕል አልዓነ<br>አማን ተንሥአ እምነ ሙታን። | ዛሬ በክርስቲያን ሰንበት ፍጹም ደስታ ሆነ፤ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ተነሥቷልና፤ ይችንም ዕለትአከበራት ከዕለታት ሁሉ ከፍ ከፍ አደረጋት፤ በውነት ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ተነስቷል።<br>ማቴ ፳፰፡ ፩-ፍጻ ፣ ራዕ ፩፡፲ |

## እስመ ለዓለም

| | |
|---|---|
| ትንሳኤከ ለእለ አመነ<br>ብርሃነከ ፈኑ ዲቤነ | ከሙታን ተለይተህ መነሳትህን እናምናለን<br>በእኛ ላይ ብርሃንህን ላክልን።<br>መዝ.፵፪፡ ፫-፬ ፡ኢሳ.፵፪፡ ፬-፮ ፡ሉቃ.፳፬፡ ፵፮-፶ ፡መዝ.፻፱፡ ፲፯-፲፰ |

## ዑደት

ትንሳኤከ ለእለ አመነ
ብርሃነከ ፈኑ ዲቤነ።

አማን በአማን አማን በአማን /2/
ኧኸ ተንሥአ እምነ ሙታን /2/

## ሰላም

ተሠሃልከ እግዚኦ ምድረከ ሃሌ ሉያ፤ ይእቲ ማርያም እምነ ወእሙ ለእግዚእነ ሰአሊ በእንቲአነ፤ ከመ ይመሃረነ ወይሰሃለነ ያስተርኢ ጊሩቱ በላእሌነ። ሰርዐ ለነ ሰንበተ ለአረፍተ ዚአነ ፍስሐ ወሰላም ለእለ አመነ።

## ጸሎተ ኪዳን

## የምስራች ቃል

ቄሱ ፦ ክርስቶስ ተንስአ እሙታን፤
ሕዝቡ፦ በዐቢይ ኃይል ወሥልጣን፤
ቄሱ ፦ አሠሮ ለሰይጣን፤
ሕዝቡ፦ አግዐዞ ለአዳም፤
ቄሱ ፦ ሰላም፤
ሕዝቡ ፦ እምይእዜሰ፤
ቄሱ ፦ ኮነ ፍሥሐ ወሰላም፤

## መዝሙር

እግዚኦ ጸወነ ኮንከነ ለትውልደ ትውልድ
ወይሰርሳ ለነ ተግባረ እደዊነ

ተፈሣሕነ ወተሐሠይነ በኲሉ መዋዕሊነ

ወተፈሳሕነ ህይንተ መዋዕል ዘአሕመምከነ
ወህየንተ ዓመት እንተ ርኢናሃ ለእኪት።
ስብሐት ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ለዓለም ወለዓለመ ዓለም።

እግዚኦ ኰነኔከ ሀቦ ለንጉሥ፤ ወይምላእ ስብሐቲሁ ኵሎ
ምድረ ለይኩን ለይኩን። ይገንዩ ቅድሜሁ ኢትዮጵያ
ወጸላእቱሂ ሐመደ ይቀምሁ።ስብሐት ለአብ ለወልድ
ለመንፈስ ቅዱስ ለዓለም ወለዓለመ ዓለም።

ግነዩ ለእግዚአብሔር እስመ ኄር፤ ወየአምር ከመ መሐሪ
እግዚአብሔር፤ ሃሌ ሉያ ንግሩ ለእግዚአብሔርምህረቶ፤
ወመንክሮሂ ለእጓለ እመሕያው፤ እስመ ሰበረ ኆኃተ ብርት
ወቀጥቀጠ መናሥግተ ዘሐጺን። ስብሐት ለአብ ለወልድ
ለመንፈስ ቅዱስ ለዓለም ወለዓለመ ዓለም።

አድኅነኒ እግዚኦ እስመ ሀልቀ ኄር፤ ወበከመ እበየ ልእልናከ
ሠራዕኮሙ ለደቂቀ እጓለ እመሕያው።

ይእዜ እትነሣእ ይቤ እግዚአብሔር፤ እሬሲ መድኃኒተ
ወአግህድ ቦቱ። ስብሐት ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ
ለዓለም ወለዓለመ ዓለም።

ሃሌ ሉያ ይትፌሣሕ ሰማይ ወትትሐሰይ ምድር፤ ወይነፍሑ
ቀርነ መሠረታተ ሕምዝ ወይወውዑ፤ አድባርወአውግር
ወኵሉ እፀወ ገዳም ወዮምሰ ዓባይ ፍሰሐ በሰማያት
ወምድርኒ ትገብር ፋሲካ ተሃጺባ በደመ ክርስቶስ።

## <u>ሰላም</u>

ተሠሃልከ እግዚኦ ምድረከ ሃሌ ሉያ፤ ፍጹመ ንጉሠ
ኰነንዎ አይሁድ ተካፈሉ አልባሲሁ ሀራ ሰባራት
ወኬርስዎ ርእሶ በሕለት ረባዝዎ ገቦሁ በኲነት
ትንሳኤሁ ገብረ በሰንበት ሰላመ ይደጉ ለነገሥት
ለአሕዛብ ወለበሐውርት ።

## <u>ጸሎተ ቅዳሴ</u>